በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የድሬዳዋ አስተዳደር
የከንቲባው ጽ/ቤት

Federal Democratic Republic of Ethiopia
Dire Dawa Administration
Mayor`s Office

☎ 025 111 1358 Fax 025 111 1072 / 0251 120073 ✉ 240 ድሬዳዋ - Dire Dawa

ቁጥር / Ref. No ድ/010-157/16

ቀን / Date 19-1-2007

ለድሬዳዋ አስተዳደር ንግድ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት ቢሮ

ለድሬዳዋ አስተዳደር መሬት ልማት ማኔጅመንት ቢሮ

ለድሬዳዋ አስተዳደር ኮንስትራክሽንና ማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት ቢሮ

ለድሬዳዋ አስተዳደር የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን

ለድሬዳዋ አስተዳደር ቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት

<u>ድሬዳዋ</u>

ጉዳዩ፡- <u>የካቢኔ ውሣኔን ለተግባራዊነቱ ማሳወቅን ይመለከታል</u>፡፡

የድሬዳዋ አስተዳደር ካቢኔ መስከረም 15 ቀን 2006 ዓ/ም ባካሄደው ስብሰባ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ቤት ፈላጊዎች በመኖሪያ ቤቶች ህብረት ሥራ ማህበር ፕሮግረም ለመመዝገብ የወጣ አፈፃፀም መመርያን በዝርዝር ከተወያየ በኋላ መርምሮ አፅድቆታል፡፡

ለአፈፃም ይረዳ ዘንድ በአስተዳደሩ የፀደቀው ይህንኑ መመርያን 13 ገፅ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን እየላክን ይኸው በናንተ በኩል ታውቆ መመርያው ተግባራዊ እንዲደረግ አስታውቃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

አሰድ ዚያድ መሐመድ
ከንቲባ

<u>ግልባጭ፡</u>

- ለኢፌዲሪ የውጭ ጉዳይ ሚ/ር
  <u>አዲስ አበባ</u>
- ለድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት
  <u>ድሬዳዋ</u>
- ለሀገር ውስጥና አለም አቀፍ አብይ የሥ/ሂደት
  <u>ከንቲባው ጽ/ቤት</u>

# በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ቤት ፈላጊዎች በመኖሪያ ቤቶች ህብረት ሥራ ማህበር ፕሮግራም ለመመዝገብ የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 11/2007

Federal Democratic Republic of Ethiopia
Dire Dawa Administration Mayer's Office

## መመሪያ ቁጥር 11/2007

## በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ቤት ፈላጊዎች በመኖሪያ ቤቶች ህብረት ሥራ ማህበር ፕሮግራም ለመመዝገብ የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት በተለያዩ ሀገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን (ዳያስፖራ) በትውልድ ሀገራቸው ሁሉ አቀፍ የልማት እንቅስቃሴ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚያስችል የዳያስፖራ ፖሊሲ ቀርጾ ተግባራዊ እንቅስቃሴ እያደረገ በመሆኑ ፣

በፖሊሲው አንቀጽ 6.5(2) እንደተጠቀሰው ዳያስፖራው በግልና በማህበር ተደራጅቶ በክልሎች፣ በአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች የቁጠባ ሥርዓትን መሠረት ያደረገ የመኖሪያ ቤት ስለሚያገኙበት ሁኔታ በጥናት ላይ የተመሰረተ አሰራር እንደሚዘረጋ በተደነገገው እና በሃገር አቀፉ የከተማ ቤት አቅርቦት ስትራቴጂ ማዕቀፍ በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በመኖሪያ ቤት የህብረት ሥራ ማህበራት በመደራጀት በመኖሪያ ቤት ልማት ፕሮግራሙ ተጠቃሚ መሆን የሚችሉበት ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበር፣ የቤት ልማት ፕሮግራም ተጠቃሚ ለመሆን የቤት ፈላጊዎች ምዝገባ በድሬዳዋ ከተማ ሲካሄድ የምዝገባ ስርዓቱ ወጥነት፣ ግልጽነትና ፍትሃዊነት ባለው መልኩ ለማካሄድ እንዲቻል የአፈፃፀም መመሪያ መውጣት እንዳለበት በመታመኑ፤

የድሬዳዋ አስተዳደር ካቢኔ በድሬዳዋ አስተዳደር የከተማ ቦታን በሊዝ ለማስተዳደር እንዲያስችል በወጣው ደንብ ቁጥር 8/2005 አንቀጽ 58 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህን የአፈፃፀም መመሪያ አውጥቶአል፡፡

Federal Democratic Republic of Ethiopia
Dire Dawa Administration Mayor's Office

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ «በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ቤት ፈላጊዎች በመኖሪያ ቤቶች ህብረት ሥራ ማህበር ፕሮግራም ለመመዝገብ የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 11/2007 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

1. «ዲያስፖራ» ማለት ከኢትዮጵያ ውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ነው፣
2. «ሃዋላ» ማለት በውጭም ሆነ በሀገር ውስጥ በሚገኙ ባንኮች ወይም የገንዘብ አስተላላፊ ድርጅቶች አማካኝነት ገንዘብ የማዘዋወሪያ ዘዴ በኢትዮጵያ የባንክ አሠራር ዕውቅና የተሰጠው ነው፣
3. «ዲፕሎማቲክ ፓውች» ማለት በቪየና ኮንቬንሽን መሠረት ለአንድ ሚሲዮን ኦፊሴላዊ ሥራ ብቻ እንዲያገለግሉ የተፈቀዱ ሠነዶች መያዣና መላላኪያ ከረጢት ነው፣
4. «ሚሲዮን» ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት በውጭ ሀገር ያቋቋመው ወይም የሚያቋቁመው ኤምባሲ ወይም ቋሚ መልዕክተኛ ጽህፈት ቤት ወይም ቆንስላ ጽህፈት ቤት ነው፣
5. «ነባር የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር» ማለት በውጭ ሀገር በሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን እንዲሁም ተመላሽ ዳያስፖራ በመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበር ተደራጅቶ በዝግ ሂሳብ ገንዘብ ያስቀመጠ፣ በማህበራት ማደራጃ የምዝገባ ሠርተፍኬት ያለውና እስካሁን ድረስ የመኖሪያ ቤት ግንባታ ቦታ ያልተረከበ የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር ነው፣
6. «አዲስ የመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበር» ማለት በማህበር በመደራጀት ታውን ሃውስ እና አፓርትመንት ቤቶችን ለመገንባት የሚፈልጉ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ለመመዝገብ የወጣው የምዝገባ ማስፈፀሚያ መመሪያ ቁጥር 1/2006 ፀድቆ ተፈፃሚ መሆን ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በአዲስ መልክ የሚቋቋም የቤት ህብረት ሥራ ማህበር ነው፤
7. «በግል ተመዝጋቢ» ማለት በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በታውን ሃውስ በተናጠል ተመዝግቦ በጋራ የመኖሪያ ቤት ተጠቃሚ የሚሆንበት ሥርዓት ነው፣
8. «የውክልና ማስረጃ» ማለት በህግ የተደነገገ ሥርዓትን ተከትሎ በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል/ውልና ማስረጃ እና ሚሲዮን በአካል ቀርቦ የተሰጠ እና በውጭ ጉዳይ ሚኒቴር እና በሠነዶች ማረጋገጫ መሥሪያ ቤት የተረጋገጠ የውክልና ሠነድ ነው፡፡

9. «ዲፕሎማት» ማለት በኢፌዲሪ ሚሲዮኖች በውጭ ግንኙነት መስክ ተመድቦ የሚያገለግል ኢትዮጵያዊ የመንግስት ሠራተኛ ነው፣
10. «ሎካል ሠራተኛ» ማለት በሀገር ቤት ተቀጥሮ በኢፌዲሪ ሚሲዮን ተመድበው እያገለገለ የሚገኝ ሠራተኛ (non-diplomatic staff) ነው፣
11. «ተመላሽ ዲያስፖራ» ማለት ለተለያዩ ምክንያቶች ወደ ሀገር ውስጥ ተመልሰው በተለያዩ ስራዎች ተሰማርተው የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ነው፣
12. «የማህበራት ማደራጃ» ማለት በድሬዳዋ አስተዳደር ንግድ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ የህብረት ሥራ ማደራጃና ልማት አብይ የሥራ ሂደት ነው፤
13. «ታውን ሃውስ» ማለት ጂ+1 ወይም ጂ+2 ወለል ያለው ራሱን የቻለ መጠነኛ ግቢ እና መግቢያ ያለው የመኖሪያ ህንፃ ሲሆን ከአጎራባች መኖሪያ ቤቶች ጋር በግድግዳ የተያያዘ መኖሪያ ቤት ነው፣

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ተፈፃሚ የሚሆነው በመንግስት አስተባባሪነትና ድጋፍ ከሚገነቡት የቤት ልማት ፕሮግራሞች ተጠቃሚ ያልሆኑ በግል ተመዝግበው በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር የሚደራጁ እና በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር ተደራጅተው ታውን ሃውስ ለመገንባት የሚፈልጉ በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን፣ በኢፌዴሪ ሚሲዮኖች ተመድበው/ተቀጥረው በስራ ላይ የሚገኙ ዲፖሎማቶች እና ኢትዮጵያዊያን ሎካል ሠራተኞች እንዲሁም ተመላሽ የዳያስፖራ አባላት ላይ ነው፣

## 4. የመመሪያው ዓላማ

1. በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በቤት ልማት ፕሮግራሙ ተጠቃሚ ለመሆን ለምዝገባ መስፈርት የሚያስፈልገውን ዝርዝር የአሰራር ሂደት ግልጽ ለማድረግ፣
2. በምዝገባ ሂደት የሚሳተፉ ባለድርሻ አካላት ተቀናጅተው እንዲሰሩ ግልጽ የአሰራር ስርዓት ለመዘርጋትና ተግባርና ኃላፊነታቸውን አውቀው መመሪያውን እንዲያስፈጽሙ ለማድረግ፣

## 5. መርሆዎች

1. በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በሚካሄዱ የቤት ልማት ፕሮግራሞች ለሀገራቸው ልማት አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ሁኔታዎች ይመቻቻሉ፣
2. ግልጽ እና ፈጣን የምዝገባ፣ የቁጠባና የአደረጃጀት ስርዓት በመከተል መረጃዎች ለሁሉም ተደራሽ እንዲሆኑ ይደረጋል፣
3. ባለድርሻ አካላት በተቀናጀና አሳታፊ በሆነ መልኩ ለጋራ ዓላማ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ተመላሽ ዳያስፖራ ለመደገፍ መንግስት እያደረገ ያለውን ጥረት እንዲያግዙ ይደረጋል፣

Federal Democratic Republic of Ethiopia
Dire Dawa Administration Mayor's Office

## ክፍል ሁለት

## ስለምዝገባ መስፈርት የምዝገባ ጊዜ እና ውክልና

### 6. በግል የመኖሪያ ቤት ተመዝጋቢዎች

በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በግል ተመዝግበው በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር ተደራጅተው በታውን ሃውስ ቤት ለመገንባት ፍላጎት ያላቸው የሚከተሉትን በማሟላት ምዝገባ ማከናወን ይችላሉ፡፡

1. የፀና የፓስፖርት ቅጂ እና የሚኖሩበት አገር የፀና የመኖሪያ ፈቃድ በተጨማሪም የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር አባልነት መታወቂያ ካርድ ቅጂ፣
2. የሌላ አገር ዜግነት ያገኙ ከሆኑ የፀና የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ቅጂ፣
3. የጋብቻ ማስረጃ ዋናውንና ቅጂውን፣
4. ሁለት ፓስፖርት መጠን ፎቶ ግራፍ፣ ወይም ያላገባ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ፣
5. ለዚሁ ጉዳይ የተዘጋጀ የምዝገባ ቅጽና ውል ሞልቶና ፈርሞ ማቅረብ፣
6. ተመዝጋቢዎች አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መንግስት በሚያወጣው ፕሮግራም መሠረት የጣት አሻራ ለመስጠት ፈቃደኛ መሆን ይገባቸዋል፣
7. በመረጡት የመኖሪያ ቤት አይነት የግንባታውን ወጪ ሙሉ ክፍያ (100 ፐርሰንት) በውጭ ምንዛሪ ከፍለው በአገር ውስጥ በሚከፈተው የባንክ ሂሳብ ገቢ ያደረጉበትን የደረሰኝ ቅጂ ማቅረብ የሚችሉ፣
8. በመረጡት የቤት አይነት የግንባታውን ወጪ 50 በመቶ ክፍያ በምዝገባ ወቅት በሚኖሩበት አገር በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በኩል የባንክ ሂሳብ በመክፈት የሚያስቀምጥና ቀሪውን 50 በመቶ መሬት ተዘጋጅቶ የመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበሩ ሲረከብ ሙሉ በሙሉ በመክፈል የግንባታ ፍቃድ ለመውሰድ ዝግጁ የሆነ እና በውጭ ምንዛሬ ከፍለው በአገር ውስጥ በሚከፈተው የብር ሂሳብ ገቢ ያደረጉበትን የደረሰኝ ቅጂ ማቅረብ የሚችሉ፣
9. ግለሰቡ እንደተደራጀ የሚቆጠረው የግንባታውን ወጪ 50 ፐርሰንት ክፍያ ፈጽሞ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡
10. ከዚህ በፊት በራሱም ሆነ በትዳር ጓደኛው ስም የመኖሪያ ቤትም ሆነ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ የሌለው ወይም ኖርት ለሶስተኛ ወገን ያላስተላለፈ፣

Federal Democratic Republic of Ethiopia
Dire Dawa Administration Mayor's Office

7. **<u>በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት የተደራጁ ቤት ፈላጊዎች</u>**

በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር የአደረጃጀት መመሪያ ቁጥር 4/2005 የተቀመጡት የአደረጃጀት፣ የምዝገባና የቁጠባ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ ፕሮግራም መሳተፍ የሚፈልጉ ማህበራት፡

1. ከዚህ በፊት በራሱም ሆነ በትዳር ጓደኛው ስም የመኖሪያ ቤትም ሆነ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ የሌለው ወይም ኖሮት ለሶስተኛ ወገን ያላስተላለፈ፣
2. በመንግስት በተዘረጉት ሌሎች የቤት ልማት ፕሮግራሞች ላይ ተጠቃሚ ያልሆነ ወይም ለመጠቀም ያልተመዘገበ ወይም ተመዝግቦም ከሆነ ምዝገባውን መሰረዙን ወይም መተዉን ግዴታ መግባት የሚችል፣
3. አንድ ማህበር በህጋዊ መንገድ በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር ለመመዝገብ የሚችለው ሁሉን የማህበሩ አባላት የግንባታ ወጪውን 50 ፐርሰንት መክፈል ሲችል ብቻ ነው፡፡
4. ማህበሩ እንደተመሰረተ የሚቆጠረው የግንባታውን ወጪ 50 ፐርሰንት ክፍያ ፈጽሞ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፣
5. የነባር ማህበራትን አመዛጋገብ በተመለከተ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው የህብረት ስራ ማህበራት ማደራጃ የስራ ክፍል ጋር በጋራ ተስማምተው በሚያቀርቡት ዝርዝር ስምምነት መሰረት የሚፈፀም ይሆናል፣
6. ሁሉም የህብረት ስራ ማህበራት የራሳቸው መጠሪያ ሲኖራቸው በመጠሪያ ማህበራት ስር ያሉ አባላት በሙሉ የሚቀርብላቸውን ቅጽ 005 በራሳቸው ወይም በወኪላቸው አማካኝነት ሙሉ በሙሉ መሙላት ይገባቸዋል፣
7. የህብረት ስራ ማህበር አባላት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መንግስት በሚያወጣው ፕሮግራም መሠረት የጣት አሻራ ለመስጠት ፈቃደኛ መሆን ይገባቸዋል፣
8. የህብረት ስራ ማህበራት የራሳቸውን የግንባታ ዲዛይን በማዘጋጀት ማቅረብ የሚችሉ ሲሆን ዲዛይኑ እንደአግባቡ የሚመለከተው አካል ሲያፀድቀው ተግባራዊ ይሆናል፣

8. **<u>በኢፌዲሪ ሚሲዮኖች ተመድበው የሚሰሩ ዲፕሎማቶችና ሎካል ሠራተኞች</u>**

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሚሲዮኖች የሚሰሩ ዲፕሎማቶችና ሎካል ሠራተኞች በከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በፀደቀው የመኖሪያ ቤት የህብረት ስራ ማህበር የአደረጃጀት መመሪያ ከተመለከቱት የምዝገባ መስፈርቶች በተጨማሪ፡-

1. የፀና የኢትዮጵያ ፓስፖርት ቅጂ እና
2. ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚሰጥ ማረጋገጫ ደብዳቤ፣

አሟልተው ምዝገባ ማከናወን ከፈለጉ በመረጡት የመኖሪያ ቤት አይነት የግንባታ ወጪውን 50 በመቶ በኢትዮጵያ ብር ከፍለው በዳያስፖራው የምዝገባ የጊዜ ሠሌዳ ተመዝግበው በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለሰው ሃብት ማኔጅመንት ዳ/ጄኔራል መላክ አለባቸው፡፡



Dire Dawa Administration Mayor's Office

## 9. ከፕሮግራሙ ስለመሰረዝ

1. በግል ተመዝጋቢም ሆነ በማህበር የተደራጀ ተመዝጋቢ የምዝገባ መመሪያውን መስፈርቶች ሳያሟላ የተመዘገበ እንደሆነ ከምዝገባ ፕሮግራሙ ከመሰረዙ በተጨማሪ አግባብ ባለው ህግ ሊጠየቅ ይችላል፣
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለፀው ቢኖርም ከማህበሩ አባላት ውስጥ አንዱ ወይም የተወሰኑት አባላት መስፈርቶችን የማያሟላ ከሆነ በግል ተጠያቂ ሆነው ማህበሩ በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት የሚቀጥል ይሆናል፣

## 10. ስለውክልና

1. ማንኛውም በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን የመኖሪያ ቤት ፈላጊ ለመመዝገብና ሌሎች ጉዳዮችን ለመከታተል በአካል መቅረብ ካልቻለ ተወካዩ መቅረብ ይኖርበታል፤
2. ተወካዩ የማህበር አባልም ሆነ የግለሰብ ተመዝጋቡውን ወክሎ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ በዚህ ማስፈፀሚያ መመሪያ የተደነገጉትን ጉዳዮች አክብሮ የመስራት ኃላፊነት አለበት፣
3. ተወካዩ የተሳሳቱ መረጃዎችን በማቅረብ ወካዩ ተጠቃሚ እንዲሆን ካደረገ እንደያልተገባ ጥቅም ተጋሪ ተቆጥሮ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሶስት

## የባንክ ሂሳብ አከፋፈት፣ የቤቶች አይነትና ምዝገባ ዋጋ

## 11. የባንክ ሂሳብ አከፋፈት

1. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለሁሉም የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራትና በግል ተመዝጋቢዎች የሚያገለግል የባንክ ሂሳብ የመክፈት አገልግሎት ብቻ ይሰጣል፣
2. የሚመለከተው የህብረት ስራ የማህበራት ማደራጃ የጋራ አካውንት( Pull account ) በመክፈት ሁሉም ማህበራት ከምዝገባው በፊት ወደዚህ ሂሳብ ገቢ እንዲያደርጉ ይደረጋል፣
3. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ገቢ የተደረገውን ገንዘብ በተመለከተ ማረጋገጫ ለማህበራት ማደራጃ ይልካል፣
4. ቤት ፈላጊ የዳያስፖራ አባላት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 ስር የተገለጹትን ሳይጨምር እንዲገነባላቸው የፈለጉትን የቤት አይነት የክፍያ መጠን በውጭ ምንዛሪ መክፈል ይኖርባቸዋል፣
5. ተመዝጋቢዎች ክፍያ የሚፈጽሙበት ሀገሪቱ በምትገበይባቸው ገንዘቦች ብቻ ይሆናል፣
6. ተመዝጋቢዎች ከዚህ በፊት በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የዳያስፖራ አካውንት ካላቸው ከዚህ ሂሳብ ወደ መኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ሂሳብ እንዲዞርላቸው ማድረግ ይችላሉ፣
7. ነባር ማህበራት ዝግ ሂሳባቸው በሌላ ባንክ ከሆነ ወደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በማዞር አዲስ የባንክ ሂሳብ በብር መክፈት ይጠበቅባቸዋል፣



Federal Democratic Republic of Ethiopia
Dire Dawa Administration Mayor's Office

8. በውጭ ሀገር የሚኖሩ በግል ተመዝጋቢዎችና በማህበር የተደራጁ የመኖሪያ ቤት ፈላጊዎች የምዝገባና የባንክ ሂሳብ የመክፈት ሂደቱን ለማስፈፀም መሟላት የሚጠበቅባቸው መስፈርቶች፣

ሀ. የፀና የፓስፖርት ቅጂ እና ከሚኖሩበት አገር የመኖሪያ ፈቃድ ወይም የኮሚኒቲ ማህበር አባልነት መታወቂያ ካርድ ቅጂ

ለ. የሌላ አገር ዜግነት ያገኙ ከሆነ የፀና የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ቅጂ፣

ሐ. ሁለት ፓስፖርት መጠን ፎቶ ግራፍ፣

መ. ለዚህ ጉዳይ የተዘጋጀውን የምዝገባ ቅጽና ውል ሞልቶና ፈርሞ ማቅረብ፣

ሠ. በመረጡት የመኖሪያ ቤት አይነት የግንባታውን ወጪ 50 በመቶ በውጭ ምንዛሬ በመላ በአገር ውስጥ በሚከፈተው የብር አካውንት ገቢ ያደረጉበትን የክፍያ ደረሰኝ ቅጂ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፣

9. በተለያየ ምክንያት በአካል በኢፌዴሪ ሚሲዮን ቀርበው መመዝገብ የማይችሉ በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በግል ተመዝጋቢና በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር የሚገነቡ መኖሪያ ቤት ፈላጊዎች በተወካዮቻቸው አማካኝነት የሚከተለውን አሟልተው መመዝገብ ይችላሉ፡፡

ሀ. የወካይ የፀና የፓስፖርት ቅጂ እና ከሚኖሩበት አገር መኖሪያ ፈቃድ በተጨማሪ የኮሚኒቲ ማህበር አባልነት መታወቂያ ካርድ ቅጂ፣

ለ. ወካይ እና ተወካይ የሌላ አገር ዜግነት ያገኙ ከሆነ የወካይ የፀና የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ቅጂ፣

ሐ. የወካዩ ሁለት ፓስፖርት መጠን ፎቶ ግራፍ፣

መ. በወካይ ስም በመረጡት የመኖሪያ ቤት አይነት የግንባታውን ወጪ 50 በመቶ በውጭ ምንዛሬ ከፍለው በአገር ውስጥ በተከፈተው የብር አካውንት ገቢ ያደረጉበትን የክፍያ ደረሰኝ ቅጂ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፣

10. በአገር ውስጥ በተለያዩ የኢንቨስትመንት፣ የንግድና የሙያ ሥራ ዘርፎች የተሰማሩና አገር ውስጥ እየኖሩ ያሉ ተመላሽ የዳያስፖራ አባላት የሚከተሉትን ሲያሟሉ ብቻ በኢትዮጵያ ብር ከፍለው ሂሳብ መክፈት ይችላሉ፡፡

ሀ. ትውልደ ኢትዮጵያውያን የሆኑ ተመላሽ የዳያስፖራ አባላትን በተመለከተ

- የፀና ፓስፖርት ዋናውንና ቅጂውን፣
- የውጭ ዜግነት ያለው ከሆነ የፀና የትውልድ ኢትዮያዊ መታወቂያ ካርድ ዋናውንና ቅጂውን፣
- አገር ውስጥ ቢያንስ ሁለት አመትና ከዚያ በላይ መኖሩን የሚያሳይ ማስረጃ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ማቅረብ፣
- በሀገር ውስጥ በአለም አቀፍ/አህጉራዊ ድርጅቶች፣ በመንግስታዊዊ መንግስታዊ ባልሆኑ እና በግል ድርጅቶች ውስጥ ተቀጥሮ የሚሰራና ወርሃዊ ክፍያው በኢትዮጵያ ብር እንደሆነና ግብር ከፋይ ፣መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ማቅረብ የሚችል፣
- በሀገር ውስጥ ሌላ የመተዳደሪያ ገቢ ካለው ይህንኑ የሚገልጽ ማስረጃ ዋናውንና ቅጂን ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ለ. ኢትዮጵያውያን የሆኑ ተመላሽ የዳያስፖራ አባላትን በተመለከተ፡-

- የፀና ፓስፖርት ዋናውንና ቅጂውን፣
- ከኖረበት አገር የፀና የመኖሪያ ፈቃድ ዋናውንና ቅጂውን፣
- አገር ውስጥ ከሁለት አመት በላይ ያለመኖሩን/ሯን የሚያሳይ ማስረጃ ዋናውንና ቅጂን ወይም፣
- በሀገር ውስጥ በአለም አቀፍ/አህጉራዊ ድርጅቶች፣ በመንግስታዊ፣ መንግስታዊ ባልሆኑ እና በግል ድርጅቶች ውስጥ ተቀጥሮ የሚሰራና ወርሃዊ ክፍያው በኢትዮጵያ ብር እንደሆነና ግብር ከፋይ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡

## 12. የሂሳብ እንቅስቃሴና የገንዘብ ዝውውር ሁኔታ

1. የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት የሂሳብ እንቅስቃሴ ሁኔታ በመተዳደሪያ ደንቡና ለመኖሪያ ቤት በዝግ ሂሳብ የተቀመጠ ገንዘብ ስለማንቀሳቀስ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጋር በሚገቡት ውልና ሂሳቡን እንዲያንቀሳቅስ በተስማሙት ህጋዊ ተወካይ ወይም የማህበሩ አመራሮች መሰረት ይሆናል፡፡
2. በግል ተመዝጋቢዎች በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አማካይነት ከሚከፈላቸው የግል አካውንት ላይ ወደ ተደራጁበት ማህበር ሂሳብ እንዲዘዋወር ከማህበራት ማደራጃ በሚደርሰው ትዕዛዝ መሠረት ይህንኑ በመፈፀም ለማህበራት ማደራጃ ያሳውቃል፡፡

Federal Democratic Republic of Ethiopia Dire D... Administration Mayor's Office

## 13. ቁጠባው ተመላሽ ስለሚደረግበት ሁኔታ

በግል ተመዝጋቢዎችም ሆነ ከመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት መኖሪያ ቤት ፈላጊዎች ምዝገባ ተሰርዞ ገንዘቡ እንዲመለስ የተወሰነ ተጠቃሚ ግለሰብ ወይም ማህበር የሚመለሰው ገንዘብ በወቅቱ ምንዛሪ በኢትዮጵያ ብር ሆኖ በቁጠባው ውሉና በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት የሚያገኘውን የወለድ ጥቅም በመጨመር ነው፡፡

## 14. የሚገነቡ ቤቶች አይነት፣ ስፋት እና የቤቶች የምዝገባ ዋጋ

በውጭ አገር በሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በግል ተመዝጋቢና የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት የሚገነቡት መኖሪያ ቤቶች ታውን ሃውስ ሲሆኑ የቤቶቹ ስፋት እና ጠቅላላ ዋጋ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

1. 1. ባለ 2 መኝታ የቤቱ ስፋት 128 ካ.ሜ ዋጋው ብር 582400.00
2. ባለ 3 መኝታ የቤቱ ስፋት 160 ካ.ሜ ዋጋው ብር 728000.00
3. ባለ 4 መኝታ የቤቱ ስፋት 200 ካ.ሜ ዋጋው ብር 910000.00
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)፣ (2) እና (3) የተጠቀሱት የግንባታ ዋጋዎች ለምዝገባ ወቅት ብቻ የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ የግንባታ ዋጋው የማጠናቀቂያ ስራዎችን በከፊል አያካትትም፣ የቦታ ዝርዝር፣ የዲዛይኖች ዝግጅትና የግንባታ ጊዜውን መሠረት በማድረግ የዋጋ ልዩነት ሊኖረው ይችላል፡፡
5. በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ምዝገባና አደረጃጀት በተለይ የማህበራት አባላት ብዛት፣ በቤት አይነት፣ በመኝታ ቤትና በህንፃ ከፍታ ተለይቶ የተቀመጠው ስታንዳርድ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

**በታውን ሃውስ G+1 እና G+2 የቤት አይነት የአባላት ብዛትና የሚያስፈልግ የቦታ ስፋት**

| አማራጭ | የቤት አይነት | የአንድ ማህበር የሚይዘው አባላት ብዛት | ለአንድ ቤት የሚሰጠው የቦታ ስፋት በሜ.ካ | የሚያስፈልግ የቦታ ስፋት በሜ.ካ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ባለ 2 መኝታ | 14 | 160 | 1920 |
| 2 | ባለ 3 መኝታ | 14 | 200 | 2400 |
| 3 | ባለ 4 መኝታ | 14 | 250 | 3000 |

## 15. <u>የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ክትትል</u>

1. በመኖሪያ ቤት ህብት ስራ ማህበር ተደራጅተው የተመዘገቡ አባላት የቤቶች ግንባታ የሚከናወኑ አስተዳደሩ ባቋቋመው የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት አማካኝነት ይሆናል፣
2. በተመሳሳይ በግል ተመዝግበው በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር ቤት ለመስራት የሚፈልጉ አባላት መንግስት በቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት አማካኝነት እንዲገነቡ ያደርጋል፣
3. ቤቶቹ ተገንብተው እስከሚጠናቀቁ ድረስ ያለውን የግንባታ ሂደት የሚከታተለው የድሬዳዋ አስተዳደር የቤቶች ልማት ፕ/ጽ/ቤት ይሆናል፤
4. በግልም ሆነ በማህበር የሚገነቡ መኖሪያ ቤቶች ከርክክብ በፊት የግንባታ አፈፃፀማቸው መቶ ፐርሰንት የተጠናቀቁ ይሆናሉ፣

## 16. <u>የመኖሪያ ቤት ርክክብና ቅድሚያ አወሳሰን</u>

1. ከዚህ በፊት በማህበር ተደራጅተው የነበሩ በውጭ ሀገር ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በድጋሚ በዚህ መመሪያ መስፈርቱን አሟልተው ከተመዘገቡ ከአዲስ ተመዝጋቢ ማህበራት ቅድሚያ መብት ይኖራቸዋል፣
2. በማህበር የተደራጁ አባላት የመኖሪያ ቤት ርክክብን በተመለከተ ማህበሩ ግንባታውን ከሚያከናውነው አካል ጋር በገቡት ስምምነት መሠረት የሚፈፀም ሲሆን ለእያንዳንዱ የማህበር አባል የቤት ርክክብ የሚፈፀመው ግን በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አማካኝነት ይሆናል፣
3. በግል የተመዘገቡ የመኖሪያ ቤት ፈላጊዎችን በተመለከተ የቤት ግንባታ የሚካሄድላቸው በጋራ ሲሆን የመረጡትን ቤት መሠረት በማድረግ በዕጣ እንዲከፋፈሉ ይደረጋል፣

Federal Democratic Republic of Ethiopia
Dire Dawa Administration Mayor's Office

# ክፍል አራት

# ተግባርና ኃላፊነት

## 17. የቤት ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት

1. በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር ተደራጅተውና እውቅና ተሰጥቷቸው ከሚመለከተው አደራጅ አካል ከሚቀርቡ የህብረት ስራ ማህበራት ጋር ስለቤቱ ግንባታ፣ ፋይናንስና ርክክብ ጉዳይ ውል ይዋዋላል፣
2. ለግንባታ የሚያስፈልገውን በዝግ የተቀመጠ የህብረት ስራ ማህበሩን ገንዘብ ግንባታውን ለመጀመር የሚያስችለውን ፋይናንስ እና ቀሪ ገንዘብም በሚቀርብ ግንባታ አፈፃፀም ደረጃ እየታየ እንዲለቀቅለት ይጠይቃል፣
3. የቤቶች ግንባታ ሲጠናቀቅ በውሉ መሠረት ለተጠቃሚዎች ያስረክባል፣
4. የህብረት ስራ ማህበራቱ በተረከቡት መሬት ላይ በአግባቡና በዲዛይኑ መሠረት የሥራ ተቋራጮችን፣ አማካሪዎችንና ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን በማሳተፍ የቤቶችን ግንባታ በተቀመጠው ስታንዳርድና ውል መሠረት በማከናወን ለአስተዳደሩ ንግድ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ የሥራ ክፍል እንዲያስረክቡ ያደርጋል፣
5. በዚህ መመሪያ አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 8 የተጠቀሰው የግንባታ ዲዛይን የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት የሚያፀድቀው ይሆናል፡፡
6. ቤቶቹ ተገንብተው እስከሚጠናቀቁ ድረስ ያለውን የግንባታ ሂደት የሚከታተል/ የሚመራ አደረጃጀት ይፈጥራል፣

## 18. ንግድ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ

1. በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን እና ተመላሽ ዳያስፖራ በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር ተደራጅተው ለመመዝገብ የሚያስፈልጋቸውን የአደረጃጀት መመሪያዎችንና ቅጾችን ያሳውቃል፣
2. የመኖሪያ ቤቱን የግንባታ ክፍያ 50 ፐርሰንት ያሟሉና ሌሎች ለምዝገባ  የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎችን መሟላታቸውን በማረጋገጥ የምዝገባ እውቅና ሰርተፍኬት እንዲያገኙ ያደርጋል፣
3. በውጭ የሚኖሩ ሆነው በምዝገባው ወቅት በአካል አገር ቤት የሚገኙ የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር አባላትን በተመለከተ በውጭ ምንዛሪ የባንክ ሂሣብ ከፍተው በአካል ቀርበው እንዲመዘገቡ ያደርጋል፣

4. የተመዘገቡና ቅድመ ሁኔታዎችን ያሟሉ የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት የቦታ ዝግጅትና ግንባታ ፈቃድ እንዲያገኙ ለአስተዳደሩ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮና ለግንባታ ፍቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን በማቅረብ እንዲፈቀድ ያደርጋል፣

5. በኢፌዲሪ ሚሲዮኖች ተመድበው የሚያገለግሉ ዲፕሎማቶችና ሎካል ሠራተኞች በመኖሪያ ቤት ህብረት የስራ ማህበራት የተደራጁ አባላት ዝርዝር መረጃ በውጭ ጉዳይ ሚኒቴር በተላከለት እና በኢትዮያ ንግድ ባንክ መረጃ መሠረት የግንባታውን ወጪ ሙሉ ክፍያ ያጠናቀቁ የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት የምዝገባ እውቅና ሠርተፍኬት እንዲያገኙ ያደርጋል፣

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

19. . በዚህ መመርያ በተደነገጉ ድንጋጌዎች መሠረት የተመዘገበው ዲያስፖራ ቁጥሩ ከፍተኛ ከሆነ የአስተዳደሩ ካቢኔ ካለው የመሬት አቅርቦት ውስንነት አንፃር ተመልክቶ አስፈላጊውን ውሳኔ ይሰጣል፡፡

20. በከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በፀደቀው ቤት ህብረት ስራ ማህበራት የአደረጃጀት መመሪያ የተቀመጡ ክልከላዎች በሙሉ በዚህ መመሪያ ተፈፃሚነት አላቸው፣

21. በከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በፀደቀው ቤት ህብረት ስራ ማህበራት የአደረጃጀት መመሪያ ላይ በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በሚመለከት ከተቀመጠው መስፈርት ውጭ መመዝገብም ሆነ እንዲመዘገብ ማድረግ የተከለከለ ነው፣

22. በዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች መሠረት ምዝገባ የሚጀመረው አስተዳደሩ መሬት ካዘጋጀ በኋላ ይሆናል፤

23. **ቅጣት**

በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር የአደረጃጀት መመሪያ ቁጥር 4/2006 እና በዚህ መመሪያ የተቀመጡትን የምዝገባ መስፈርቶች ሳያሟላ የተመዘገበ እና ክልከላዎችን የተላለፈ፣ ለመመዝገብ የሞከረ ወይም ሀሰተኛ መረጃ በማቅረብ የተመዘገበ ማንኛውም ተመዝጋቢም ሆነ የተመዝጋቢ ተወካይ አግባብ ባለው የወንጀለኛ እና የፍትሐብሔር ህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

24. **መመሪያውን ስለማሻሻል**

ይህን መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ የአስተዳደሩ ካቢኔ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

## 25. ተፈፃሚ የማይሆኑ ህጎች

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያና የተለመደ አሰራር በዚህ መመሪያ ውስጥ በተካተቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## 26. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በአስተዳደሩ ካቢኔ ከፀደቀበት ከመስከረም 15 ቀን 2007 ዓም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ድሬዳዋ መስከረም 15 ቀን 2007 ዓ/ም**

**አሰድ ዚያድ**

**የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ**